የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)
Ethiopian Peoples Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

# ከወክንድ የተሰጠ መግለጫ

ህዳር 21 ቀን 2007 ዓ.ም

## ፀረ- ወያኔው ትግል ይፋፋም!

የወያኔን ጸረ-ዴሞክረሲያዊንት ለማስረገጥ ሐቁ ሞልቶ መፍሰስ ከጀመረ ብዙ ዓመታትን አስቆጠረ። ወያኔ ለህግ የበላይነት ይገዛል ብሎ ማስብ ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመመኘት ይሆናል ብንል ማጋነን አይሆነብንም። ወያኔ ከፍጥረቱ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ከሐቅ ተጣልቶ፣ ሀሰተን አንግሶ፣ ጥላቻን ተላብሶ በማደናገርና በማወናበድ ፓሊሲ የተመራ በመሆኑ አሁንም እድሜውን ጨርሶ በማብቂያው አዝማሚያ ያላደገበትን፣ ያልለመደውን ፍትህና ዴሞክርሲያዊ ባህሪ እንዲያሳይ ልንጥብቅ ከቶ አይግባም።

እኛ ወያኔ ከነግሳንግሱ ወደ ታሪክ ትቢያ እንዲወርድ ከመታገል ሌላ አማራጭ የለም ብለን በፅኑ የምናምንና በቀቢፀ ተስፋ የተሞላን ሰላልሆን፣ ከወያኔ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫን አንጠብቅም። ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል እንዲሉ ወያኔና ሐቅ ሁሌም ለየቅል መሆናቸውን ጠንቅቀን እናውቃልንና ። ዴሞከሪሲ ስንል የህዝብ ልዕልና፣ ነጻ ዳኝነት፣ የህግ የበላይነት፣ የሰብዓዊ መብቶች መረጋገጥና የዜጎች እኩልነት እውን መሆን ማለት ነው። የወያኔ ዴሞክራሲ ጭንጋፍ ሳይሆን ጨርሶ የማይፀነስ ለመሆኑ የህክምና መዝገበ-ቃላትን መግለጥ ከቶም አያይሻም ።

ወያኔ ለዴሞክራሲ መካን መሆኑ ለተለጣፊዎችና ለታማኝ ተቃዋሚዎች አልከሰት ያለ በሽታ ቢሆንም ለሀገርና ወገናቸው በሚታገሉ ዜጎቿ ግን ከታወቀ ዘመናትን አስቆጥሮአል። የዴሞክራሲ መገለጫው ህዝብ ወሳኝ ሆኖ በሀገሩ ጉዳዮች ፍላጎቱ ሲንጸባረቅና መብቶቹ ሲከበሩለት ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደህዳር በሽታ ለወያኔ ዘረኛ ወረርሽኝ ተጋልጣ ህልውናዋ በየቀኑ እየተሸረሸረ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ወያኔ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን አላቅቆ፣ ገነጣጥሎና አሽመድምዶ ሊያጠፋት የቆመ ሀይል መሆኑን ማውቅና መገንዘብ ተገቢ ነው።

ራሱን ያወቀ ጠላትን ያወቀ ነው። ስለሆነም ለምን እንደሚታገል፤ ማንን እንደሚታግልና እንዴት መታገል እንዳለበት የተረዳ ብቻ ነው አሸናፊ ሊሆን የሚችለው። ስለትግል ስናወራ የወያኔን አፈጣጠርና ባህሪ መረዳት ይኖረብናል። ተጨባጭ እውነታዎችን ሳያድበሰብሱ መመልከት፤ መመርመረና መገንዝብ ያሻል። ወያኔ ትናንት የደረሰበት ደረጃ ላይ የደረሰው ብቻውን ባደረገው ጥረት አይደለም። እስዛሬም እድሜው የረዘመው በውጭ ጠላት አጋዥነትም ሆነ በእነ ስብሃትና በረከት ተዋናይነት ብቻ ሳይሆን "የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ" በሚሉ እበላ ባዮች፤ አገር አዋራጆችና አስምሳዮች በመብዛታቸው ነው ብንል ከሀቅ የራቅን አይመስለንም።

ዛሬም ከ24 ዓመት በኋላ በወያኔ ሙሉ ቁጥጥር ሥር በሚካሄድ ምርጫ ስለመሳተፍ የሚያላዝኑ "ፖለቲከኞች" መድረኩን ማጣበባቸው ሳይገርመን፣ በምርጫ ሥም የዴሞከረሲያዊ ምርጫን መመዘኛ ማንሳት እርኩስ ለአሪዎስ እንደሆነ የሚሰብኩና ለወያኔ ራሱን በራሱ የመምረጥ ቲያትር ተዋንያን የሆኑ ዛሬም አሉ። አንዳንዶቹ እንዲያውም የወያኔ አይነተኛ መርዝ የሆነውን ጎሰኝነት እንዳለ ገልብጠው እንደ አዲስ ራዕይ እያስፋፉ ወጣቱንም በዚሁ መረባቸው ለማጥምድ

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com

ሲወራጩ መታየታቸው ገሀድ ነው። ሌሎች ደገሞ ትግልና ንግድ ተወራራሽ ሆኖባቸው በትግል ሥም ለመከብር ደፋ ቀና ሲሉ የታያል።

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጲያ ህዘብ ክመቼውም ጊዜ በከፋ የኑሮና የፍትህ እጦት እየተሰቃይ መሆኑ ግልፅ ነው። ህዝቡ የኑሮ ውድነቱን መቋቋም አልቻለም። መላ ሀገራችንን ለጥፋት ለመዳረግ በሥልጣን ላየ የተሰየመው አገዛዝ በመሠረቱ ጸር-ህዝብ መሆኑ የሚጠበቅ ቢሆንም፣ በህዝብና በአገር ላይ የሚያደርሰውን በደል ማውገዝ፣ የህዝቡን ትግል ማገዝና እንደቀደምቶቹ የኢሕአወሊ ወጣቶቸ በትግሉ ወላፈን ውስጥ በግንባር  ቀደምትነት መካፈል፣ የእኛ የወጣቶች ታሪካዊ ሃላፊነትና ግዴታም ጭምር መሆኑን ኢህወክንድ እንደገና መግለጥ ይወዳል ።

በኢህአወሊ ሰማዕታት ደም የተጻፈውን ታሪክ ወራሽ የሆነው ኢወክንድ ፀረ- ወያኔው ትግል በሁሉም ዘርፍ እንዲፋፋም ለአገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ወጣቶች እንስባስብ ብሎ የትግል ጥሪውን ያቀርባል።  ትግሉን በቆራጥነት ለመግፋት የተነሱ፣ ከጥቅጥቅ ጨለማ ባሻገር የንጋት ጮራ እንደሚፈነጥቅ፣ ካንዣበበው የክረመት ደመና ፀደይ እንደሚወለድ የሚያውቁ በርካታ ወጣቶች ሀገራቸን ኢትዮጵያ ዛሬም  አላት።

ፀረ-ወያኔው ትግል የፋፋም!

ድል የሕዝብ ነው!!

Tel: 202-291-5832 5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
E-mail: eprpylnew @gmail.com Website: www.eprpyl.com